አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር - 11/2011 ዓ.ም
Issue No. 11, 2019

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# AWASH NEWSLETTER




- የዋና ሥራ አስፈፃሚ መልዕክት.................................................... 2
- የ5ተኛው ዙር የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማበረታቻ የሎተሪ ዕጣ አሸናፊዎች ሽልማታቸውን ከባንኩ ተቀበሉ................................... 3
- ማሕበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የተለያዩ ሥራዎች ተከናወኑ........ 4
- ለዳያስፖራው ማሕበረሰብ ልዩ የባንክ አገልግሎት ተዘጋጀ............... 5
- 23ኛው የባለአክሲዮኖች ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ተካሄደ.................. 6
- ጃክሮስ ቅርንጫፍን ከዘረፋ ያዳኑ ሠራተኞች ተሸለሙ..................... 7
- Agreement Signed.............. 7


በማርኬቲንግና ኮምዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by Marketing & Communication Directorate

Customer Line 8980 Tel.:+251-11557 00 00/0167 Fax:+251-11557 01 36
P.O.Box 12638 Addis Ababa, Ethiopia E-Mail: contactcenter@awashbank.com
Website: www.awashbank.com Swift Code: AWINETAA





**አቶ ፀሐይ ሽፈራው**
የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ

## በዓመቱ ለተመዘገቡት አመርቂ ውጤቶች ለመላው የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች እንኳን ደስ አላችሁ እያልኩኝ  እንዲሁም መላው የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች የስኬታችን መሰረት መሆናቸውን እየገለጽኩ በተገኘው ውጤት ሳንዘናጋ ለበለጠ አመርቂ ውጤት በአዲስ መንፈስ እንድንነሳ ጥሪዬን ለባንኩ የስራ አመራር አባላት እና ሠራተኞች ለማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

# የዋና ሥራ አስፈጻሚው መልዕክት

**መላው የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች የስኬቶቻችን መሰረት ናቸው!**

እንደሚታወቀው እ.ኤ.አ. 2017/18 የነበረውን የሂሳብ ዓመት ባንካችን በሁሉም የፋይናንሻል ሁኔታ አመላካቾች በመሪነት ማጠናቀቁ ለባንኩ ማህበረሰብ ትልቅ የሞራልና የመነቃቃት ስሜትን ፈጥሯል፡፡ ከዚህ አኳያ በዓመቱ የተመዘገቡት ስኬቶችና ድሎች ልዩ የሚያደርጋቸው አብዛኞቹ ስራዎች ከዕቅድ በላይ መመዝገባቸው ነው፡፡

ለአብነት ያህልም የፋይናንስ አፈፃፀምን በተመለከተ የባንኩ ጠቅላላ ተቀማጭ ሂሳብ ኤልሲ ማርጅንን ጨምሮ እ.ኤ.አ ሰኔ 2018 መጨረሻ ላይ ብር 45.9 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ ይህም አሃዝ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ40 በመቶ ወይም የብር 13 ቢሊዮን ጭማሪ አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል ባንካችን ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ከብር 5.4 ቢሊዮን በላይ ገቢ አግኝተቷል፡፡


ይህ አጠቃላይ ገቢ ካለፈው የሂሳብ ዓመት ጋር ሲነፃፀር ከብር 1.7 ቢሊዮን በላይ ወይንም የ44 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ከጠቅላላው ገቢ ውስጥም ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ከወለድ የተገኘው ገቢ ሲሆን ይህም ከጠቅላላው ገቢ 78 % ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የባንካችን ጠቅላላ ወጪ  ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር  1 ቢሊዮን ወይንም የ41 %  ዕድገት አሳይቷል፡፡

ባንካችን በተገባደደው ሂሳብ ዓመት በትርፍ ረገድም አመርቂ ውጤት ያስመዘገበ ሲሆን የባንካችን ያልተጣራ ትርፍ ብር 1.96 ቢሊዮን ሲሆን ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የብር 650 ሚሊዮን ወይም የ49.5%  እድገት ተመዝግቧል፡፡ ይህም በሀገሪቱ ካሉት የግል ባንኮች ከፍተኛው  የትርፍ መጠን ያደርገዋል፡፡

ስለሆነም በዓመቱ ለተመዘገቡት አመርቂ ውጤቶች ለመላው የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች እንኳን ደስ አላችሁ እያልኩኝ እንዲሁም መላው የአዋሽ ባንክ ቤተሰቦች የስኬታችን መሰረት መሆናቸውን እየገለጽኩ በተገኘው ውጤት ሳንዘናጋ ለበለጠ አመርቂ ውጤት በአዲስ መንፈስ እንድንነሳ ጥሪዬን ለባንኩ የስራ አመራር አባላት እና ሠራተኞች ለማስተላለፍ እወዳለሁ፡፡

በአጠቃላይ ባንካችን አሁን ባለው አፈፃፀም በምስራቅ አፍሪካ ካሉት ምርጥ 10 ባንኮች ተርታ ለመሰለፍ በ10 ዓመቱ ፍኖተ ካርታ ላይ ያስቀመጠውን ግብ ለማሳካት በሚያስችለው ቁመና ላይ እንደሚገኝ አመላካች ነው፡፡ በያዝነው ዓመትም ማለትም እ.ኤ.አ 2018/19 በተለመደው የአዋሽ ባንክ ባህል እንደ አንድ አካል ሆነን እጅ ለእጅ ተያይዘን ያስቀመጥነውን  ግባችንን ለማሳካት በአንድነት መንፈስ እንድንሰራ ከአደራ ጭምር አሳስባለሁ፡፡

በተጨማሪም የባንኩን የ10 ዓመት ፍኖተ ካርታ ለማሳካት ሁሉም የባንኩ ቤተሰቦች ያለሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በተለይ በደንበኞች አገልግሎት ላይ ጠንካራ ስራ መስራት አለብን፡፡



# የአምስተኛው ዙር የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማበረታቻ የሎተሪ ዕጣ አሸናፊዎች ሽልማታቸውን ከባንኩ ተቀበሉ

- ለአንደኛ እጣ የተዘጋጀው አይሱዙ የጭነት መኪና ጅማ ከተማ ገብቷል!
- የስድስተኛው ዙር ከአዋሽ ይቀበሉ ያሸንፉ መርሐ ግብር በይፋ ተጀምሯል!




**አቶ ሀሰን አባገሮ አባጊሳ**
የመኪናውን ቁልፍ ሲረከቡ

ባንኩ የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን ለማሳደግ አቅዶ ከዚህ በፊት ሲያካሄዳቸው የነበሩት አራት መርሐ-ግብሮች በሙሉ በተሳካ ሁኔታ የተከናወኑ ሲሆን ከነሐሴ 21 ቀን 2010 እስከ ሕዳር 20 ቀን 2011 ዓ.ም የቆየው የአምስተኛው ዙር "ከአዋሽ ይቀበሉ! ያሸንፉ!" የሎተሪ ሽልማት መርሐ-ግብር ታሕሳስ 9 ቀን 2011 ዓ.ም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ድርጅት አዳራሽ ተሸላሚ ባለዕድለኞችን የመለየትና ዕጣ የማውጣት ስነ-ስርዓት በህዝብ ፊት ይፋ ተደርጓል፡፡

ታህሳስ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በሒልተን አዲስ አበባ ሆቴል በተደረገው የሽልማት ስነ-ስርዓት የባንኩ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው እንደተናገሩት ባንኩ የውጭ ምንዛሪ አቅሙን ለማጎልበትና የውጭ ሀገር ገንዘቦች በሕጋዊ መንገድ እንዲመነዝሩ ለማድረግ "ከአዋሽ ይቀበሉ ያሸንፉ" በሚል መርሐ ግብር ባለዕድለኞችን ሲሸልም መቆየቱ አስታውሰው ይህም በሀገሪቱ የሚስተዋለውን ጥቁር ገበያ ለመከላከል በሚደረገው እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፆ እንደሚኖረው አስገንዝበዋል፡፡

የአምስተኛው ዙር የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ መርሐ-ግብር ለየት የሚየደርገው እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ባንካችን ካዘጋጃቸው የማበረታቻ ሽልማት በተጨማሪ የሀገሪቱ መንግስት የውጭ ሀገር ገንዘቦችን በባንክ የመመንዘር ጥሪ ተከትሎ ቁጥራቸው በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች ወደ አዋሽ ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብና የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች በመሆን የሽልማት እድላቸውንም ጭምር ለማስፋት መቻላቸው እንደሆነ ተስተውሏል፡፡

በ5ኛው ዙር ተዘጋጅተው የነበሩት የሽልማት ዓይነቶች በሶስት ምድቦች የተከፋፈሉ ሲሆን፣ ለአንደኛ ዕጣ የተዘጋጀው የሽልማት ዓይነት አይሱዚ የጭነት መኪና ተሸላሚ የጅማ ከተማ ነዋሪ አቶ ሀሰን አባገሮ አባጊሳ የመኪናውን ቁልፍ ከባንኩ ከፍተኛ የስራ አመራሮች በዕለቱ ተረክበዋል፡፡

በሽልማት ስነ-ስርዓቱ ላይ በአዲስ አበባ ለሚገኙ የ2ኛ እና የ3ኛ ዕጣ አሸናፊዎች የተዘጋጀላቸውን የቴሌቪዥን እና የውሃ ማጣሪያ ተቀብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ባንኩ ስድስተኛውን ዙር "ከአዋሽ ይቀበሉ ያሸንፉ" መርሐ-ግብር ከታህሳስ 20 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በማካሄድ ላይ ሲሆን የባንኩ ደንበኞችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም የውጭ ሀገራት ገንዘቦችን በአዋሽ ባንክ ቅርንጫፎች በመገኘትና በመመንዘር እንዲሁም በዓለም አቀፍ ገንዘብ አስተላላፊዎች በኩል በተጨማሪም በባንኩ Swift ኮድ በኩል የተላከላቸውን ገንዘብ በመቀበል የተዘጋጀላቸውን ሽልማት ማለትም:-

1ኛ. ዕጣ አንድ 15 ሰው መጫን የሚችል ዘመናዊ መኪና፣

2ኛ. ዕጣ ሶስት ዕጣዎች እያንዳንዳቸው ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ፣

3ኛ. ዕጣ አምስት ዕጣዎች እያንዳንዳቸው ልብስ ማጠብያ ማሽኖች

4ኛ. ዕጣ አስር ዕጣዎች እያንዳንዳቸው የውሃ ማጣርያዎች ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ለሁሉም ደንበኞች የባንኩ ዋና የስራ አስፈፃሚ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



# አዋሽ ባንክ የኮርፖሬት ማሕበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወኑን ገለጸ

- ባንኩ በምዕራብ ኢትዮጵያ ለተፈናቀሉ ወገኖች ማቋቋምያ የ15 ሚሊዮን እንዲሁም በጣና ሃይቅ የተከሰተውን እምቦጭ አረም ለመከላከል የሚውል የ10 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል

አዋሽ ባንክ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ የማህበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት የተለያዩ ሥራዎችን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን በቅርቡም ከምዕራብ ኢትዮጵያ ለተፈናቀሉ ወገኖች ማቋቋሚያ የሚውል ብር 15 ሚሊዮን ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ያስረከበ ሲሆን፣ በጣና ሐይቅ ላይ የተከሰተውን የእንቦጭ አረም ለማጥፋት ይረዳ ዘንድ ደግሞ ብር 10 ሚሊዮን በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኩል ማበርከቱ ይታወሣል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታህሳስ 16 ቀን 2011 ዓ.ም ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንዲሁም ከፍተኛ የባንኩ የስራ ሀላፊዎች በተገኙበት በሒልተን አዲስ አበባ ሆቴል በተደረገው ሥነ-ሥርዓት ደግሞ ለሰባት ሀገር በቀል ግብረሠናይ ድርጅቶች የተመደበውን የብር 5 ሚሊዮን የገንዘብ እርዳታ ለድርጅቶቹ ኃላፊዎች አስረክቧል። በዚሁ መሰረት፡

1. ሞት በኩላሊት ይብቃ በጐ አድራጐት ማህበር

ለዚህ ማህበር የተለገሰው የገንዘብ መጠን ብር 1.6 ሚሊዮን ሲሆን ገንዘቡ የተለገሰው ለአራት የኩላሊት ማጠቢያ ማሽኖች ግዥ እንዲውል ታስቦ ነው።

2. ጌርጌሴኖን የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማህበር

ለዚህ ግብረሠናይ ድርጅት የተለገሰው የገንዘብ መጠን ብር 800,000.00 /ስምንት መቶ ሺህ/ ሲሆን ገንዘቡ የሚውለው በድርጅቱ ማዕከል ውስጥ ላሉት 600 ተረጂዎች የምግብ፣ የመጠለያና የሕክምና ወጪ መሸፈኛ የሚሆን ነው።

3. ሁንዴ ኦሮሞ ግራስሩትስ ደቨሎኘመንት ኢኒሼቲቭ

ለዚህ ግብረሠናይ ድርጅት የተለገሰው የገንዘብ መጠን ብር አንድ ሚሊዮን ሲሆን ገንዘቡ የተለገሰው የገጠር ሴቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማሳደግ ለተነደፈው ኘሮጀክት ማስፈጸሚያ እንዲውል ነው።

4. የወደቁትን አንሱ የነዳያን መርጃ ማህበር

ይህ ድርጅት በሰብአዊ አገልግሎት ላይ የተሰማራ ሲሆን ጧሪና ቀባሪ ያጡትን ከየጐዳናው በመሰብሰብ በአሁኑ ወቅት ዘመናዊ ማዕከል በመገንባት ከመቶ በላይ ለሚሆኑ ተረጂዎች የሕክምናና የምግብ አገልግሎት የሚውል ብር 600,000.00 / ስድስት መቶ ሺህ እርዳታ ተደርጎለታል ።

5.ጉርሙ ዴቨሎኘመንት አሶሴሽን

ይህ ግብረሠናይ ድርጅት የገጠር ሴቶችን የጤና እና የኢኮኖሚ ገቢ ለማሻሻል የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ሲሆን ማህበሩ ለነደፈው የሴቶች የዶሮ እርባታና የገበያ ትስስር ማስፈጸሚያ የሚውል የብር 350,000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ እርዳታ ተደርጐለታል።

6. ኪድስ ኬር ማሕበረሰብ አቀፍ አገልግሎት


ይህ ማህበር በአሁኑ ወቅት ትምህርት ቤት በመገንባት የአቅመ ደካሞችንና ልጆቻቸውን ለማስተማር ለማይችሉ ወላጆች የትምህርት አገልግሎት በአዲስ አበባ እና በደብረብርሃን በመስጠት ላይ ይገኛል።

ለዚህ ድርጅት የተሰጠው የገንዘብ መጠን የብር 350,000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ሲሆን ገንዘቡ የሚውለው ለ40 የተማሪዎች ወንበር እና 60 የመመገብያ ጠረጴዛዎች መግዣ ነው።

7. ሶሳይቲ ፎር ፎረስት ላንድስኬፕ ሬስቶሬሽን ኤንድ ኮንሰርቬሽን

ይህ ሀገር በቀል በጐ አድርጐት ማህበር በአካባቢ ጥበቃና ደን ልማት ተግባር ላይ የተሰማራ ሲሆን በደን የተራቆቱትን አካባቢዎች መልሶ ለማልማት ለነደፈው ለችግኝ ማፍላት እና ለተለያዩ የዛፍ ዝሪያ መረጣ ኘሮጀክት የሚውል የብር 300,000.00 /ሶስት መቶ ሺህ/ እርዳታ ተደርጐለታል።

ባንኩ በቀጣይም የተለያዩ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶችን እንዲሁም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በፋይናንስ በመደገፍ ማህበራዊ ሀላፊነቱን ለመወጣት በቁርጠኝነት እንደሚሰራ በዚህም ለሌሎች ተቋማት ፋና ወጊ እንደሚሆን ጭምር የባንኩ ዋና የስራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው በሥነ-ሥርዓቱ ላይ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።



# አዋሽ ባንክ ለደያስፖራው ማሕበረሰብ ልዩ ልዩ የባንክ አገልግሎቶችን ማዘጋጀቱን አበሰረ!

በኢትዮጵያ የባንኪንግ ሴክተር አገልግሎት ከግል ባንኮች መካከል የመጀመሪያው እና ፈር ቀዳጅ የሆነው አዋሽ ባንከ በመላው ዓለም ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን ታሳቢ ያደገረ ልዩ የባንክ አገልግሎቶችን ተግባራዊ አድርጓል።

ከነዚህ አገልግሎቶች መካከል ዜጐች በሚኖሩበት ሀገር በውጭ ምንዛሪ የተለያዩ ተቀማጭ ሂሳብ መክፈት የሚያስችል ይገኝበታል። ደንበኞች በጊዜ ገደብ የተቀመጠውን ዝቅተኛውን መጠን ይኸውም 5,000 ዶላር በሚያስቀምጡበት ጊዜ የአለም አቀፍን የወለድ ምጣኔ ጣሪያ ግምት ውስጥ በማስገባት ለባንኩና ለደንበኛው የጋራ ስምምነት ላይ የተመሰረተ ጠቀም ያለወለድ አዘጋጅቷል። በተንቀሳቃሽ ሂሳብ አገልግሎትም ሂሳቡ ተንቀሳቃሽ ሆኖ ወለድ የማይከፈልበት ሲሆን ደንበኞች ገንዘባቸውን በማንኛውም ሰዓት ቼክ በመጻፍ ወጪ ማድረግ ያስችላቸዋል። ይህ የቁጠባ ሂሳብ አስቀማጮች የገቢ ንግድ አገልግሎትን በተቀላጠፈ መልኩ ማከናወን ያስችላቸዋል።

በተጨማሪም ወደ ውጭ ሀገር ሂሳብ ወይም ገንዘብ ማዘዋወር በማይችለውና በብር በሚቀመጥው አገልግሎቱ ባንኩ ዜጐች ከውጭ ሀገር በሚልኩት ገንዘብ ወደ ሀገር ውስጥ ገንዘብ ተቀይሮ በብር የሚቀመጥበትንና በሀገር ውሰጥ የተለያዩ ክፍያዎችን ለመፈጸም የሚያገለግል አገልግሎት ሲሆን በዚህ ሂሳብ ላይ ደንበኞች ከመደበኛው የተቀማጭ ሂሳብ እጥፍ የሆነ የወለድ ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ባሻገር ባንኩ በመላው ዓለም ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የዲያስፓራው ማሕበረሰብ በሙሉ የለፉበት ህይወት እና ያለሙት ራዕይ ይሳካ ዘንድ የተለያዩ የብድር አማራጮችን ያዘጋጀ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የደያስፖራውን ማሕበረሰብ የቤት ባለቤት ለማድረግ ባዘጋጀው የመኖሪያ ቤት ግዢ እና ግንባታ የሚውል በአነስተኛ የወለድ ተመን እና በረዥም የክፍያ ዘመን የሚጠናቀቅ ሲሆን ይህንንም እውን ለማድረግ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ የቤት አልሚዎች /ሪል እስቴት/ ድርጅቶች ጋር በጋራ ተቀናጅቶ በመስራት ላይ ይገኛል።

> **የደያስፖራውን ማሕበረሰብ የቤት ባለቤት ለማድረግ ባዘጋጀው የመኖሪያ ቤት ግዢ እና ግንባታ የሚውል በአነስተኛ የወለድ ተመን እና በረዥምየክፍያ ዘመን የሚጠናቀቅ ሲሆን ይህንንም እውን ለማድረግ በአሁኑ ወቅት ከተለያዩ የቤት አልሚዎች /ሪል እስቴት/ ድርጅቶች ጋር በጋራ ተቀናጅቶ በመስራት ላይ ይገኛል።**

ከዚህም ባሻገር ለተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች፤ ለአውቶሞቢል ግዥና ለግል ፍጆታ የሚውል ብድር ይኸውም ለት/ቤት ለሕክምና ለቤተ መገልገያ እቃዎች ግዥ እና ሌሎችም የብድር አማራጮችን በዝቅተኛ የወለድ መጠን አዘጋጅቷል።

ከዚህም ጎን ለጎን ከወለድ ነፃ የባንከ አገልግሎቶችን ተጠቃሚዎች ታሳቢ ያደረገ የሙራሀባ የብድር አገልግሎት አማራጭን ያዘጋጀ ሲሆን በሂደቱም ደንበኞች የመኖሪያ ቤት ወይም የንግድ ቤት መግዥያ እና መስሪያ እንዲሁም የኢንቨስትመንት መጀመሪያ ወይም ማስፋፊያ እና ሌሎች አማራጮችን የያዘ ነው።

በመጨረሻም አዋሽ ባንክ ለመላው የዲያስፖራው ማሕበረሰብ ኑ፤ ያለሙትን ራዕይ በጋራ ሰርተን እውን እናድርገው በማለት ጥሪውን እያቀረበ አገልግሎቶቹንም ለማግኘት በሚቀርባቸው የአዋሽ ባንክ ቅርንጫፎች ወይም በአቅራብያቸው ባለ አገር ኢምባሲዎች ወይም የቆንጽላ ጽ/ቤት ቀርበው የበለጠ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

አዋሽ ባንክ በአሁኑ ጊዜ ከ 375 በላይ ቅርንጫፎች ያሉትና ባለፈው በጀት ዓመት መዝጊያ በትርፍ ፣በብድር ፤በተቀማጭ ሂሳብ፣ በሀብት እና በሌሎችም መስፈርቶች ከግል ባንኮች መሪነቱን ማስቀጠል የቻለ ጠንካራ የግል ባንክ ነው!



# የአዋሽ ባንክ 23ኛው ዓመታዊ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እና 15ኛ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ተካሄደ

- ባንኩ ወደ ሁለት ቢሊዮን ብር የተጠጋ ትርፍ በማስመዝገብ በሀገሪቱ ከሚገኙ የግል ባንኮች የመሪነት ስፍራውን በአስተማማኝ ሁኔታ አስቀጥሏል








**አቶ ታቦር ዋሚ የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በጉባኤው መክፈቻ ላይ ንግግር ሲያደርጉ**

አዋሽ ባንክ ኅዳር 15 ቀን 2011 ዓ.ም. በሒልተን አዲስ አበባ ሆቴል ባደረገው ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ እንዳስታወቀው፣ በ2010 ሒሳብ ዓመት አመርቂ ውጤት ማስመዝገቡንና በተለያዩ የባንክ አገልግሎቶች ያገኘው ጠቅላላ ውጤት በግል ባንኮች ታሪክ ከፍተኛው የሚባልና ልዩነቱንም እያሰፋ ስለመሆኑ የባንኩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ አቶ ታቦር ዋሚ በሪፖርታቸው ላይ ገልጸዋል።

ባንኩ በኢንዱስትሪው ውስጥ አዳዲስ ታሪኮች አስመዝግቦበታል ተብሎ ከተገለጸው ውስጥ አንዱ ዓመታዊ የትርፍ መጠን ዕድገት ነው።

በሒሳብ ዓመቱ ከታክስ በፊት 1.96 ቢሊዮን ብር ያተረፈ ሲሆን፣ እስከዛሬ በአገሪቱ የግል ባንክ እንቅስቃሴ ውስጥ ያልተመዘገበ ከፍተኛው ትርፍ ነው። ይህም አዋሽ ባንክ በ2009 ከታክስ በፊት ካገኘው ትርፍ በ2010 ያገኘው ከ650 ሚሊዮን ብር በላይ ብልጫ እንዳለው ያመላክታል።


የባንኩ ትርፍ እዚህ መድረስ ባንኩ የመሪነቱን ርቀት በከፍተኛ ደረጃ እንዳሰፋው የተናገሩት አቶ ታቦር፣ በቪዥን 2025 ፕሮጀክት በአሥር ዓመት ከተያዘው ዕቅድ ውስጥ በሁለተኛው ዓመት እንዲተገበርና ከታቀደው ዕቅድ በላይ ማከናወን መቻሉን የሚጠቁም ስለመሆኑም ተናግረዋል።

በአጠቃላይ የባንኩ የተጣራ ትርፍ ታክስ ከተከፈለ በኋላ 1.49 ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ይህ የተጣራ ትርፍ መጠን በባንኩና በሌሎች የአገሪቱ የግል ባንኮች ታሪክ ውስጥ የመጀመርያውና ከፍተኛ ውጤት ነው ብለዋል።

በተቀማጭ ገንዘብ ረገድም ባንኩ ከሁሉም የግል ባንኮች የላቀ የአፈጻጸም ልዩነት ያሳየ ሲሆን፣ ኤልሲ ማርጅንን ጨምሮ በ2010 ሒሳብ ዓመት የተቀማጭ ገንዘቡ መጠን 45.9 ቢሊዮን ብር ደርሷል። ይህም በአንድ ዓመት ብቻ የ13.1 ቢሊዮን ብር (40 በመቶ) ጭማሪ ያሳየ ሲሆን፣ ከፍተኛ የሚባል ስኬት እንደሆነ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ገልፀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የአዋሽ ባንክ ባለአክሲዮኖች በቀጣዩ ዓመት አዳዲስ የቦርድ አባላትን ለመሰየም ከወዲሁ የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን መርጧል። በዚህ አስመራጭ ኮሚቴ ውስጥ የቀድሞው የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የነበሩት አቶ ወሌ ጉርሙም ተካትተዋል።

በሌላ በኩል በጉባኤው ማጠቃለያ የተለያዩ የውሳኔ ሃሳቦች የተላለፉ ሲሆን የተወሰኑ የባንኩ አክስዮኖች ወደፊት በሚወጣ መመዘኛ መሰረት ለባንኩ ሠራተኞች እንዲሸጥ ተወስኗል።



# ጃክሮስ ቅርንጫፍን ከ ዘረፋ ያዳኑ ሠራተኞች ተሸለሙ

የአዋሽ ባንክ ጃክሮስ ቅርንጫፍን ለመዝረፍ የተደረገውን ሙከራ በከፍተኛ መስዋዕትነት ያከሸፉት የባንኩ የጥበቃ ሠራተኞች የምሥጋና ምሥክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት ተበረከተላቸው።



አቶ ፀሐይ ሽፈራው የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ለሠራተኞቹ የምስጋና የምስክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት ሲያበረክቱ

መሳሪያ የታጠቁ ዘራፊዎች ታህሳስ 1 ቀን 2011 ዓ.ም. ከላይ በተጠቀሰው የባንኩ ቅርንጫፍ ላይ የተቃጣውን የዘረፋ ሙከራ በዕለቱ ተረኛ ጥበቃ የነበሩት፤ አቶ መስፍን ሞገስና አቶ ብርሃኑ ሁንዴ ሕይወታቸውን ለአደጋ በማጋለጥ የታለመውን ዘረፋ ለማክሸፍ ለፈጸሙት ገድል የባንካችን ዋና-ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራውና ሌሎች የባንኩ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ሥነ-ሥርዓት የምሥጋና የምሥክር ወረቀትና የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

ሽልማቱን በዓርያነት ለሚጠቀሱት ሠራተኞች ያበረከቱት ዋና- ሥራአስፈጻሚው፤ የተቃጣውን ዘረፋ ያከሸፉትን ሠራተኞች ከማመስገናቸውም በላይ የእነሱን ዓርያነት በመከተል ሌሎችም የባንኩ ሠራተኞች በተመደቡበት የሥራ ዘርፍሁሉ ባንኩን ከጥቃት በመከላከል፤ የባንክ ሙያ ሥነምግባርን መላበስእንዳለባቸውአሳስበዋል።

# Awash Bank Inks Contractual Agreement with Finastra

Awash Bank and Finastra signed a contractual agreement for the grand upgrading of the existing core banking platform. The contractual agreement was signed by the Chief Executive Officer of the Bank, Ato Tsehay Shiferaw and Finance Director MEA & APAC of Finastra, Mr.Tony Aherne, both the signatories have explained their honor and satisfaction for this important mutual cooperation .



The Contractual Agreement Signing  Ceremony

Speaking after signing the agreement Ato Tsehay  said that such service contract would lead the bank to high level of performance and capacity in using core banking technology as  the best approach to embrace the current global banking technology.

Finastra is a Financial Technology Company led by Chief Executive Officer, Simon Paris.















# 6ኛ ዙር

**ከአዋሽ ይቀበሉ!ያሸንፉ!!**

- 1ኛ ዕጣ አንድ ዘመናዊ ሚኒባስ መኪና
- ሶስት (3) ዕጣዎች እያንዳንዳቸው ባለሶስት እግር ተሽከርካሪ፣
- አምስት (5) ዕጣዎች እያንዳንዳቸው ልብስ ማጠቢያ ማሽን
- አስር (10) ዕጣዎች እያንዳንዳቸው የውሃ ማጣሪያዎች



የዕጣው ጊዜ:- ከታህሳስ 20 ቀን 2011 ዓ/ም ጀምሮ

**ያስተውሉ!** በባንካችን በኩል አገልግሎቱን በተጠቀሙ ቁጥር ተጨማሪ የዕጣ ቁጥሮችን በመቀበል የሽልማት ዕድልዎን ያስፉ!

ለተጨማሪ መረጃ:- 8980 ይደውሉ::